# በመጀመር ላይ፡
# Joy School English



Joy School English ን ስናስተዋውቃችሁ በታላቅ ደስታ ነው፣ እንግሊዝኛን እንዲሁም ማህበራዊ እና ስሜታዊ እሴቶችን በገፀ ባህርይ ግንባታ አማካኝነት ለማስተማር በመቶዎች የሚቆጠሩ ሙዚቃዎችን፣ ቪዲዮዎችን፣ መፅሀፍትን፣ እንዲሁም አዝናኝ ጌሞችን የሚጠቀም ምርጥ የዲጂታል ፕሮግራም ነው። ይህን አዲስ ፕሮግራም በትምህርት ቤቶች ላይ እንደ ቋንቋ ካሪኩለም የምንጠቀምበት ይሆናል፣ እንዲሁም በግል መሳሪያቾሁ ላይ አፕሊኬሽኑን በመጫን በቤታችሁ ውስጥም መማር ትችላላችሁ።.

## ዝግጁ፣ ጀምር፣ ሂድ!

ለመጀመር ቀላል ነው! Joy School English ን በቤታችሁ ውስጥ ለመጠቀም እነዚህን ቀላል ደረጃዎች ይከተሉ፤

1. **Joy School English** አፕሊኬሽንን ከአፕ ስቶር ያውርዱ

   ወይም፣ በክሮም ቡክ፣ በ ፒሲ፣ ወይም በ ማክ፣ ለመጠቀም የክሮም ብራውዘርን ይጠቀሙ እና ወደ **play.joyschoolenglish.com** ይሂዱ




2. Joy School English ይክፈቱ እና የ Joy School English QR ኮዱን ከስልክዎ ካሜራ ትይዩ አድርገው በመያዝ ስካን ያድርጉ።




3. **አሁን ለመጀመር ዝግጁ ነዎት!**

- የ QR ኮድ ከሌለዎት፣ በአረንጓዴው **SCHOOL LOGIN** ትር ላይ ክሊክ ያድርጉ እና የክፍልዎን ኮድ ያስገቡ፤ ____________________.
- **ENTER**, የሚለውን ይጫኑ እና የክፍሉ ተማሪዎች ዝርዝር ውስጥ ስምዎን ይምረጡ።
- በትምህርት ቤት ውስጥ የሞሉትን ምስላዊ የይለፍ ቃል (የቅርፅ + የቀለም + የቁስ) ተጠቅመው ልጅዎ ሎግ ኢን እንዲሉ/እንዲገቡ ያድርጓቸው እና ለመግባት የይለፍ ቃል ምልክቱን ወደ በሩ ይጎትቱ እና ይጀምሩ። ለወደፊቱ የልጅዎን የይለፍ ቃል እንዲፅፉ እንመክራለን። ልጆችዎ የይለፍ ቃላቸውን ከረሱ፣ መምህራቸውን መጠየቅ ይችላሉ።










ማስታወሻ፤ ከእያንዳንዱ ክፍለ ጊዜ መጨረሻ በኋላ ልጅዎ የ አቁም/**Pause** በተንን በላይኛው ግርጌ ላይ ጠቅ በማድረግ **Log Out** የሚለውን በመምረጥ እንዲወጣ ያድርጉ። ይህ በትምህርት ቤት ክፍለ ጊዜ እና በቤት ውስጥ ክፍለ ጊዜ ውስጥ እመርታውን ከመከታተል ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመቀነስ ይረዳል።



የበለጠ ለማወቅ **joyschoolenglish.com** ን ይጎብኙ

# Joy School Englishን በመጫወት ላይ

**ተግባራት**

ልጅዎ እንግሊዝኛን የሚያስተምሩ እና የማህበራዊ እና የስሜት ክህሎቶችን የሚደግፉ የተለያዩ አይነት ተግባራትን የሚጫወት ይሆናል። እነዚህም የቃላት መዝገብን ከሚያብራሩ አጫጭር ቪዲዮዎች፣ እስከ ልምምድ ጌሞች፣ እስከ መዝሙሮች ወይም ሌሎች የንግግር መለማመጃዎች፣ እስከ የተማራቸውን ቃላት እና ሀረጎት እንዲሰርጹት የሚረዱ የተረት መፅሀፍትን ያጠቃልላል። ተግባራቶችም በመደበኛነት ከ 1-2 ደቂቃ የሚቆዩ ሲሆኑ የንግግር፣ የማዳመጥ ክህሎት፣ የጀማሪ ትምህርት፣ እና ሌሎች እሴቶችን ያጠቃልላሉ።




**የድምፅ ልየታ**

Joy School English በሺዎች የሚቆጠሩ ልጅዎ እንዲናገር የሚያደርጉ እድሎችን ፈጥሯል! በአብዛኛው ልጅዎ በስክሪኑ ግራ ጎን ላይ የድምፅ ሜትር የሚያይ ይሆናል - ይህ ማለት ፕሮግራሙ እያዳመጠ ነው እና የልጅዎን ምላሽ እየጠበቀ ነው ማለት ነው። ምናልባት ከጊዜ ጋር በተያያዘ ወይም ማይክራፎኑን በማይዘጋ መልኩ እንድትይዙላቸው የእናንተን ድጋፍ ይፈልጉ ይሆናል። ስልኩ/መሳሪያው ልጅዎ ሲያወራ በደንብ መስማት ከቻለ፣ ውጤቱም የተሻለ ይሆናል።



**የማር እንጀራ እና የንብ ቀፎ**

ልጅዎ በተግባራቱ ላይ ጥያቄዎችን ሲመልስ፣ በአብዛኛው የማር እንጀራ ሲያገኙ ትመለከታላችሁ። ይህ ሽልማት በስክሪኑ የቀኝ ጎን በልጅዎ የማር እንጀራ ሜትር ላይ ይጨመራል፣ እና በማር እየሞላው ይሄዳል። የላይኛው ጫፍ ላይ ሲደርስ፣ ልጅዎ ወደ የንብ ቀፎ የጉዞ ሽልማት ያገኛል! ይህ የሽልማት ስፍራ በጨዋታዎች እና ልጅዎ ከሚመርጣቸው የቀድሞ ተግባራት የተሞላ ነው። ከሶስት ደቂቃዎች በኋላ ወደ መደበኛው የትምህርት መስመር የሚመለስ ይሆናል፣ በእርግጥ የማር ቀፎውን በፈለጉት ጊዜ ለቅቀው መሄድ ይችላሉ።




**በየዕለቱ መጠቀም**

በዚህ ዕድሜ ላሉ ልጆች፣ Joy School English በየዕለቱ ከ 10 - 15 ደቂቃ እንዲጠቀሙ ይመከራል። በየዕለቱ ሊጠቀሟቸው የሚገቡ መደበኛው ቅንብር አስር ተግባራትን ነው (ይህ በንብ ቀፎ ውስጥ የምታሳልፋትን ጊዜ አያካትትም)፣ ይሁን እንጂ መምህርዎ ሌላ ገደብ ሊመርጥ ይችላል። ተማሪዎ በዕለቱ መጠቀም ያለባቸውን ካጠናቀቁ በኋላ፣ የ **Good Job!** ስክሪን የሚያዩ ይሆናል። ወደ ኖርማል የትምህርት መስመራቸው ነገ መመለስ ይችላሉ፣ ወይም ለመከለስ ነፃ ከሆኑ የክለሳ ዝርዝር በተኑን ጠቅ በማድረግ መከለስ ይችላሉ። ምንም እንኳ ተማሪዎች ጌሞችን ያለምንም ገደብ የመከለስ ነፃነቱ ቢኖራቸውም፣ ቤተሰቦች በኤሌክትሮኒክ ዲቫይስ አጠቃቀም ላይ ነገሮችን ከግምት እንዲያስገቡ በጥብቅ እንመክራለን። ከኤሌክትሮኒክ መሳሪያዎች ላይ ጤናማ የሆነ ግንኙነት በጣም ጠቃሚ እንደሆነ እናምናለን።

በቀን ከ **10 - 15** ደቂቃ




**የክለሳ ዝርዝር**

ተማሪዎ **የክለሳ ዝርዝርን** ማግኘት የሚችሉት በዕለቱ መጠቀም ያለባቸውን ትምህርት ካጠናቀቁ በኋላ ነው። ተማሪዎች ያጠናቀቁት ማንኛውም ተግባር ለክለሳ ዝግጁ ይሆናል። እነዚህ ወላጆች ስለ አጠቃላይ ካሪኩለሙ እና ይዘቶቹ ተስማሚ ስለመሆናቸው እንዲያውቁ በምድብ በምድብ የተደራጁ ናቸው። ይኸውም ልጆች አዲስ ክህሎታቸውን ለወላጆች እንዲያሳዩ ትልቅ ዕድል የሚፈጥር ነው።

